# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ዜና መጽሄት

# Debre Markos University Newsletter

በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ
የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
በየወሩ የሚታተም

Monthly Newsletter
Published by the Corporate
Communications Directorate

ቅጽ-3 ቁጥር-18 የመስከረም ወር 2007 ዓ.ም እትም Volume-3 Number-18 September 2014

በ2007 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን ከ380,000 በላይ የኤሌክትሮኒክስ መጽሐፍቶችን በሶፍት ኮፒና 132,114 መጽሐፍትን በሦስቱ ቤተ መጽሐፍቶች በማደራጀት ---------------------------------------- 2

ተማሪዎች የሀገራቸውን ታሪክ ጠንቅቀው እንዲያውቁ፣ ሀገራችን የምትገኝበትን ሁኔታ እንዲረዱና ለወደፊቱ ------------ 4

ተማሪዎች የተለያየ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ቀለምና አመለካከት ያላቸው ስለሆኑ እርስ በእርስ በመከባበርና በመቻቻል ለውጤት መብቃት --- 6

ሁሉም ተማሪዎች በቂ ምግብ፣ የህክምና፣ የማማከር፣ የስፖርትና መዝናኛ እንዲሁም የመኝታ አገልግሎት ለመስጠት --------- 9

ዩኒቨርሲቲው የአካባቢውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ ለማድረግ እንደ ስነምህዳሩ ሁኔታ እያደረጋቸው ያሉ እንቅስቃሴዎች ሊበረታቱ ይገባል ------------------------------------------ 12

ከኢንቨስትመንት ስራው ባሻገር የምርምር ሳይት፣ ለስራ አጦች ደግሞ የስራ እድል እየፈጠረና በተፈጥሮ ሀብት አያያዝ ከፍተኛ ሥራ እየሰራ -------------------------- 13

## በውስጥ ገፆቻችን

የ2007 ዓ.ም. የመጀመሪያው የአመራር ፎረም ተካሄደ ..................................... 1

የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም አድማሱን እያሰፋ እንደሚገኝ ተገለጸ ........................

የ2006ዓ.ም. አፈፃፀም ግምገማና የ2007 ዓ.ም. እቅድ ትውውቅ ተካሄደ ..........................

የጤናና ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ የስርዓተ ትምህርት ፍተሻ አካሄደ ........................ 5

አዲስ ለተቀጠሩና ከትምህርት ለተመለሱ መምህራን ስልጠና ተሰጠ ........................

አዲስ ለተቀጠሩ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጥበቃና ፕሮክተር ሰራተኞች ስልጠና ተሰጠ.... 6

ለአዲስ ገቢ የማታ ተማሪዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልእክትና ስለኮሌጆች አሰራር ገለፃ ተደረገላቸው ...................... 7

# ራዕይ

# Vision

## እ.ኤ.አ. በ2030 ከዓለም ካሉ ታዋቂ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ሆኖ መገኘት፡፡

Debre Markos University aspires to be world class University in 2030.

# ተልዕኮ

# Mission

## ጥራቱን የጠበቀ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ማፍራት

Producing competent and innovative professionals through providing quality instructional, CoCurricular and cultural involvement.

## አጋር አካላትን በማሳተፍ ችግር ፈች ጥናትና ምርምር ማድረግ፣

Carrying out problem solving research through the active involvement of stakeholders and,

## ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የማማከርና የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ለሃገራችን ልማት የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ፣

Providing demand driven community and consultancy services.



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: misgepower@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

# የ2007 ዓ.ም. የመጀመሪያው የአመራር ፎረም ውይይት ተካሄደ

በሁሉንአየን ጋሻው

ደ/ማ/ዩ፡- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አመራር ፎረም የመስከረም ወር ስራ አፈፃፀምን ከቅድመ ዝግጅት ጀምሮ በዳይሬክቶሬቶች፣ በየኮሌጆችና በትምህርት ክፍሎች የተከናወኑ ተግባራትንና ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን ገመገመ፡፡



የአመራር ፎረም ውይይቱ ሲካሄድ

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ፣ በአመራር ፎረሙ የ2006 ዓ.ም. አፈፃፀም ግምገማን መሰረት በማድረግ የ2007 ዓ.ም. ዕቅድ ዝግጅትና ትውውቅ፣ የክረምትና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ስልጠና፣ ግብዓት የማሟላት ተግባራት፣ የአዲስና የነባር ተማሪዎች ቅበላ፣ የዋቢ መጽሐፍትን የማሟላት ስራ፣ የመምህራንና ሰራተኞች በዝውውርና በቅጥር የማሟላት ስራና በአስተዳደር ዘርፍም በርካታ ስራዎች መካሄዳቸውን ገልፀዋል፡፡

በመቀጠልም በቅድመ ዝግጅትና በመስከረም ወር የአከናዎኗቸውን ተግባራት ሪፖርት ያቀረቡት ሁሉም ኮሌጆች የሰው ሃይልና ግብዓቶችን ለማሟላት ሲንቀሳቀሱ መቆየታቸውን ገልጸዋል፡፡

የአካዳሚክ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር አቶ ታደሰ ጤናው፣ በበኩላቸው የትምህርት አጀማመሩ ላይ የሱፐርቪዥን ስራ እንደተሰራና ሁሉም የትምህርት ክፍሎች ትምህርት በአግባቡ አለመጀመራቸውን ጠቁመዋል ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ማብራሪያ የሰጡት ዶክተር ጥላዬ ሁሉም የትምህርት ክፍሎች የመስከረም ወር የሥራ አፈፃፀምን በመገምገም ትምህርቱን በታቀደለት ጊዜ አግባብ ለመስጠትና የተሻለ ውጤት ለማምጣት መሰራት ይገባል ብለዋል፡፡



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: misgepower@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲውን ሳቢና ማራኪ ለማድረግ፣ ምቹ የመማሪያና መመራመሪያ ማዕከል እንዲሆን፣ የዩኒቨርሲቲውንና የአካባቢው ማህበረሰብ ግንኙነት ማጠናከር፣ መልካም አስተዳደርን ማስፈን፣ ሙስናንና ኪራይ ሰብሳቢነትን መታገል፣ ለመልካም አፈፃፀም ማበረታቻ መስጠትና ዩኒቨርሲቲውን ምጡቅ ምሩቃን የሚወጡበት ማድረግ በዋናነት የአመራር ፎርሙ አባላት ተልኮ መሆን እንደሚገባው አሳስበዋል፡፡

በመቀጠልም ተሳታፊዎች በመስከረም ወር አፈፃፀም ግምገማ ላይ አስተያየቶችን ሰጥተዋል፡፡ በሰጡት አስተያየትም የዩኒቨርሲቲው የግቢ ውበት ስራ ሊበረታታና ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው ነው ብለዋል፡፡ አንዳንድ የግዥ ፍላጐቶችም በጥቅል ቢቀርቡ፣ በርና መስኮቶቹ ፍርግርግ ቢሰራላቸው የተሻለ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በ2007 ዓ.ም. በ 1 ለ 5 አደረጃጀትና በልማት ቡድኖች የ2006 ዓ.ም. ተሞክሯቸውን በመጠቀም የተሻለ መስራት እንደሚቻል ተገልጿል፡፡ ሌላው መምህራን በመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ ከ10-30 ደቂቃዎችን ስለሚያባክኑ ይህን ማስተካከል እንደሚገባና የቢሮ ጽዳትም በአግባቡ የተሟላ መሆን እንደሚገባው ተጠቁሟል፡፡

በመጨረሻም የጥቅምት ወር የትኩረት አቅጣጫዎች ሁሉን አቀፍ የሙስናና የኪራይ ሰብሳቢነት ትግል ማድረግ፣ ሰላማዊ የመማር ማስተማር እንዲሰፍን ማድረግ፣ ሴኩላሪዝም ሙሉ በሙሉ እንዲተገበር ማድረግ፣ የበጀት አጠቃቀምና አስተዳደርን ማስተካከል፣ ወቅታዊና ተዓማኝነት ያለው መረጃና ስርዓትና ወቅታዊ ሪፖርት በየደረጃው ማቅረብ መሆናቸውና ሁላችንም የድርሻችንን ለመወጣት በተደራጀ መልኩ ተግባራትን መፈፀም እንደሚገባ ዶ/ር ጥላዬ ገልፀዋል፡፡

በዚህም የትምህርት ስርዓታችንን አጠናክረን በመቀጠል የጥቅምት ወር የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ውጤት ማስመዝገብ እንደሚገባ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡ የአመራር ፎረሙ ዓላማ የግቢውን የአሰራር ሁኔታ በየጊዜው እየተገናኙ በመገምገም የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመለየት ወደ ተግባር እንዲለወጡ ማድረግ መሆኑ የሚታወስ ነው፡፡

## የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም አድማሱን እያሰፋ እንደሚገኝ ተገለጸ፡፡

የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም አድማስ እየሰፋ መሆኑ ተገለጸ፡፡ እንደ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተከታታይ ትምህርት ማስተባበሪ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ይኸይስ አረጉ ገለጻ ቀደም ባሉት ዓመታት በዋናው ግቢ ውስጥ ብቻ ተወስኖ የነበረው የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም ከባለፈው

የ2006 ዓ.ም ጀምሮ በቡሬ ካምፓስ መሰጠት ጀምሯል፡፡ በዚህም ዩኒቨርሲቲው ለቡሬና አካባቢው ነዋሪዎች የትምህርት እድል መፍጠር ችሏል፡፡ እንደ እርሳቸው ገለጻ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነትን ለማስፋት በያዝነው የ2007 ዓ.ም በብቸና በላይ ዘለቀ የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ትምህርት ቤት ቅርንጫፍ ማስተማሪያ ማዕከል ከፍቷል፡፡ በዚህም የኒቨርሲቲው ጥራት ያለው ትምህርት በመስጠት ብቁና ተፎካካሪ ባለሙዎች የማፍራት ተልዕኮውን በስፋት እንዲወጣ አድርጎታል፡፡

እንደ አቶ ይሽይስ ገለጻ ዩኒቨርሲቲው በ2007 ዓ.ም ብቻ በዋናው ግቢ በማህበረሰብ ጤና አጠባበቅ፣ በነርሲንግ፣ በአዋላጅ ነርስ፣ በኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ፣ በሲቪል ምህንድስና፣ በኮንስትራክሽን ቴክኖሎጅ ማኔጅመንት፣ በኤሌክትሪካል ምህንድስና፣ በማኔጅመንት፣ በአካውንቲንግና ፋይናንስ እንዲሁም በኢኮኖሚክስ ትምህርት መስኮች ስልጠና ለመስጠት ተማሪዎችን ተቀብሏል፡፡ በብቸና ማስተማሪያ ማዕከልም በአማርኛ፣ በሲቪል ምህንድስና፣ በኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ፣ በማኔጅመንት፣ በአካውንቲንግና ፋይናንስ እንዲሁም በኢኮኖሚክስ ትምህርት መስኮች ተማሪዎችን ተቀብሎ በማስተማር ላይ ይገኛል፡፡ በቡሬ ካምፓስም በነርሲንግ፣ በአዋላጅ ነርስ፣ በኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ፣ በሲቪል ምህንድስና፣ በማኔጅመንት እንዲሁም በአካውንቲንግና ፋይናንስ ትምህርት ክፍሎች ተማሪዎችን ተቀብሏል፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ማብራሪያ ዩኒቨርሲቲው በ2007 ዓም ከ3,470 በላይ አዲስ ተማሪዎች የተመዘገቡ ሲሆን፣ በአጠቃላይም ከ5,550 በላይ የማታ ፕሮግራም ተማሪዎችና ከ8,000 በላይ የክረምት ተማሪዎች በአጠቃላይ ከ13,550 በላይ ተማሪዎችን በማስተማር ላይ ይገኛል፡፡

እንደ አቶ ይሽይስ ገለጻ የተከታታይ ትምህርት ተማሪዎች ቁጥር እያደገ ቢመጣም በዳይሬክቶሬቱ ሥር ያሉ ሰራተኞች ቁጥር ማነስ፣ የግብዓት ችግርና ኮሌጆችና ትምህርት ክፍሎች ለሥራው ዝቅተኛ ትኩረት መስጠት ችግሮች ተስተውለዋል፡፡ በመሆኑም ለትምህርትፕሮግራሙ ስኬት ሁሉም አካላት ትኩረት ሊሰጡት ይገባል ብለዋል፡፡

## የዩኒቨርሲቲው የ2006 ዓ.ም. አፈፃፀም ግምገማና የ2007 ዓ.ም. እቅድ ትውውቅ ተካሄደ

**በሰሎሞን አበበ**

**ደ/ማ/ዩ፡-** የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ መምህራንና ሰራተኞች በ2006 ዓ.ም. የአፈፃፀም ግምገማ እና በ2007 ዓ.ም. እቅድ ዙሪያ ትውውቅ በማድረግ ውይይት አካሔዱ፡፡ ፕሮግራሙን በንግግር

የከፈቱት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ እንዳሉት ዩኒቨርሲቲው ያዘጋጀው እቅድ መነሻው ከእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ ላይ ነው፡፡

እንደ እርሳቸው ገለጻ ዩኒቨርሲቲው የ2006 እቅድ አፈጻጸምን ገምግሞ የ2007 ዓ.ም እቅድን ያዘጋጀው በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ነው፡፡ እቅዱን በየደረጃው ባሉ አካላት ለማስገምገምና የጋራ ግንዛቤ ለመውሰድ በሀገር አቀፍ ደረጃ በነበረው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ስልጠና ፕሮግራም መደራረብ ምክንያት እስከ ዝግጅት ምዕራፉ ማጠናቀቂያ ሊዘገይ ችሏል፡፡ ሆኖም የዩኒቨርሲቲውን ተልዕኮዎች ለማሳካት ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በእቅዱ ዙሪያ የተሟላ እውቀትና መረጃ በመያዝ እንዲሁም በዋና ዋና አቅጣጫዎች ላይ ግንዛቤ በመፍጠር እቅዱን ከአመራር እስከ ፈፃሚው የጋራ መግባባት ይዞ የበኩሉን እንዲወጣ ለማድረግ ውይይቱን ማካሄድ አስፈልጓል በማለት ገልፀዋል፡፡



የ2007 ዓ.ም. ዕቅድ ትውውቅ ከፊል ገጽታ

የአፈፃፀም ግምገማውንና የእቅድ ትውውቁን ያቀረቡት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ እንደገለፁት ዩኒቨርሲቲው ሲመሰረት ሦስት መሰረታዊ ተልዕኮዎች ተሰጥተውታል፡፡ ተልዕኮዎቹን ለማሳካት የተዘጋጀው እቅድም የዩኒቨርሲቲው የአምስት ዓመት ስትራቴጅክ እቅድ፣ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድና ከ2006 ዓ.ም. አፈፃፀም መነሻ በማድረግ መዘጋጀቱን አብራርተዋል፡፡

እንደ ዶ/ር ንጉሴ ማብራሪያ በ2006 ዓ.ም. የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ቦርድ የተሻለ አፈፃፀም ነበረው፡፡ እቅድ አውጥቶ ይሰራ ነበር፣ በየሦስት ወሩ አፈፃፀሙን በመገምገም አቅጣጫ ያስቀምጥ ነበር፣ ስራ እና ኃላፊነቶችንም በመከፋፈል ማከናወኑ በአውንታዊ ጐኑ ሊጠቀስ ሲችል፣ ነገር ግን በአሉታዊ ጐኑ የቦርድ አባላት ተሟልቶ ያለመኘት ችግር ተስተውሏል በማለት አክለው ገልፀዋል፡፡



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: misgepower@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

ከፍተኛ አመራሩ ስልጠና ወስዶ ወደ ስራ መግባቱ፣ የአገልግሎት አሰጣጡ ተገልጋዩን የሚያረካ እንዲሆን ስራዎች መሰረቱ በአውንታዊነት፣ ዩኒቨርሲቲው ውስጥ የመተካካት ስራ በመስራት ረገድ ውስንነት ማስተዋሉ በአሉታዊነት ተጠቅሷል፡፡ መካከለኛ አመራሩ ስልጠና ወስዶ ወደስራ ቢገባም ስራዎችን ቆጥሮ መስጠት እና መረከብ ላይ ውስንነት ነበር፣ ክራይ ሰብሳቢነትንም ከመዋጋት አንፃር እጥረቶች ተስተውለዋል፡፡ ዝቅተኛ አመራሩ የትምህርት ብክነትን በተመለከተ አበረታች ስራ ሰርቷል ነገር ግን ተግባራትን ቆጥሮ መስጠትና ቆጥሮ መቀበል እንዲሁም መገምገም ዙሪያ ውስንነቶች ተስተውለዋል በማለት ምክትል ፕሬዚዳንቱ አውስተዋል፡፡ በተጨማሪም አብዛኛው መምህር ተልኮውን ለማሳካት ደፋ ቀና የሚል ቢሆንም አንዳንዶች ደግሞ የተመደበላቸውን ክፍለ ጊዜ የማይጠቀሙ፣ ተዘጋጅው ወደ ክፍል የማይገቡ እና የትምህርት ልማት ሰራዊት አደረጃጀቱ ጠቀሜታ ሌላ ነው ብለው የሚያስቡም መስተዋላቸው እንዲሁም በፆታዊ ትንኮሳ ተግባራት በጣም ጥቂቶች መሳተፋቸው በአሉታዊ ጐኑ የሚጠቀስ ነበር፡፡ ከሰራተኞች አንፃርም አንዳንድ ሰራተኞች ሆን ብለው አገልግሎት የሚያጓድሉ፣ ችግሮች ሲፈጠሩ የሚያባብሱ ቁጥራቸው እናሳ ቢሆንም መስታዋሉን ምክትል ፕሬዚዳንቱ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

እንደ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ማብራሪያ በ2007 ዓ.ም. የሚከናወኑ ቁልፍ ተግባራት የትምህርት ልማት ሰራዊት በመገንባትና የለውጥ ስራዎችን በመተግበር የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ ሲሆን ይህን ቁልፍ ተግባር ለመፈፀም የሚከናወኑ ተግባራትም በዝግጅት ምዕራፍ ግብዓት ማሟላት፣ እቅድ ትውውቅና ግምገማ ማድረግ፣ የቡሬ ካምፓስን ርክክብ መፈፀም፤ አዲስ የሚገቡ ተማሪዎችን እና መምህራንን ኦሬንቴሽን መስጠት፤ የፕሮጀክት ግንባታ መስሪያቤቱን በሰው ሃይል ማሟላት ዋና ዋናዎች መሆናቸው ተብራርቷል፡፡

የ2007 ዓ.ም. እቅድ ግቦችም የተማሪዎችን የውድድር አቅምና የፈጠራ ችሎታ ማዳበር፣ የትምህርት ፕሮግራሞችን አግባብነት ማሻሻል፤ አዳዲስ የትምህርት ፕሮግራሞችን መክፈት፤ የርቀት ትምህርት መጀመር፤ የመማር ማስተማር ሂደቱን አሳታፊ ማድረግ፤ የመምህራን እና ሰራተኞችን አቅም ማሳደግ፤ ግብዓቶችንና አቅርቦቶችን ማሻሻል፣ ጥራት ያላቸው ጥናትና ምርምሮች ለማህበረሰቡ ማቅረብ፣ የዩኒቨርሲቲውን ሀብትና ንብረት በትክክል ስራ ላይ እንዲውል ማድረግ፤ የዩኒቨርሲቲውን ገቢ ማስገኛ ስራዎች ማጠናከር፤ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓቱን አርኪ እንዲሆን ማድረግ፤ የሰራተኞችን ተሳትፎ ማሳደግ፤ የግንኙነት ስትራቴጅዎችን ማሻሻል፣ ምቹ የስራ አካባቢ መፍጠር እና የደንበኞችን አጋር አካላትን እርካታ ማሳደግ እንደሆኑ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ጠቅሰዋል፡፡

በመጨረሻም የተለያዩ ጥያቄዎች ከተሳታፊዎች ተነስተው በምክትል ፕሬዚዳንቶች ምላሾች ተሰጥቷቸዋል፡፡ ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት በማጠቃለያ ሃሳባቸው እንዳሉት መልካም አስተዳደር በአንድ ተቋም የህግና የበላይነት ማስፈን መሆኑን፣ ግልፀኝነት በአገልግሎት አሰጣጣችን ያለምንም ልዩነት ማስፈን እንደሆነ፣ በአሳታፊነት መርህ ተማሪዎች፣ መምህራንና ሰራተኞች በዩኒቨርሲቲው ጉዳዮች ተሳታፊ መሆናቸው የሚረጋገጥበት እንደሆነ፣ በፍትሃዊነት በፆታ፣ በብሔርና ሌሎችም ልዩነት ሳይፈጠር ሚዛናዊ አልግሎት አሰጣጥ መተግበሩ የሚረጋገጥበት እና በተጠያቂነት መንፈስ ተገቢውን ምላሽ መስጠትም እንደሆነ በአጽንኦት ገልፀዋል፡፡

ዶ/ር ጥላዬ ጌታ ጨምረው እንደተናገሩት ሰላማዊ የመማር ማስተማር እንዲሰፍን ለሰላማዊ መማር ማስተማር ጠንቅ የሆኑ ጉዳዩችን እየፈታን መሄድ እንዳለብን፣ በዩኒቨርሲቲው ሴኩላሪዝም እንዲሰፍን የመማር ማስተማር ሒደቱ ከባህል፣ ከፖለቲካ እና ከሃይማኖት ተጽእኖዎች ነፃ እንዲሆን መስራት እንደሚገባም ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ በማጠቃለያ ጨምረው አሳስበዋል፡፡

## የጤናና ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ የስርዓት ትምህርት ፍተሻ አካሄደ

በሁሉንአየን ጋሻው

ደ/ማ/ዩ፡- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጤናና ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ በሶስት የትምህርት ክፍሎች (አዋላጅ ነርሲንግ፣ ማህበረሰብ ጤና፣ ነርሲንግ) እና አዲሱ የህክምና ትምህርት ቤት ስርዓተ ትምህርቶች ላይ በፍኖተ ሰላም ከተማ የስርዓት ትምህርት ፍተሻ አካሄደ፡፡



የስርዓት ትምህርቱ ፍተሻ አጀማመር ከፊል ገጽታ



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: misgepower@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

የዩኒቨርሲቲው የጤናና ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ ዲን አቶ ጌታቸው ሃይሉ የስርዓት ትምህርቱን ፍተሻ በንግግር ሲከፍቱ እንደገለፁት የስርዓት ትምህርቱ ፍተሻ ዓላማ አራቱን የትምህርት ክፍሎች ኮርሶችን በመፈተሽ በይዘቶች፣ በኮርሶች ቅደም ተከተል፣ በኮርሶቹ መካከል ያለውን የእርስ በእርስ ትስስር እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን በመቃኘት የማስተካከያ ሃሳቦች በማምጣት ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ ነው፡፡

በስርዓት ትምህርት ክለሳውም የተካተቱት አራቱ የትምህርት ክፍሎች፣ የአዋላጅ ነርሲንግ፣ የነርሲንግ፣ የማህበረሰብ ጤናና አዲሱ የህክምና ትምህርት ቤት መምህራን ተማሪዎቻቸውን ሲያስተምሩ በጋራ የሚሰሯቸው በርካታ ተግባራት ስላሉ ለጋራ ስኬት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ገልፀዋል፡፡ ሌላው አላግባብ የተካተቱ ይዘቶችን በሙያው ባለቤቶች ግምገማና እይታ የሚጨመሩ ወይም መውጣት የሚገባቸውን ነጥቦች ለመለየት ያስችላቸዋል ብለዋል፡፡

የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ደሳለው አባዋ በበኩላቸው የስርዓት ትምህርት ፍተሻ መደረጉ የይዘቱን ስፋት፣ አግባብነት፣ ልንፈጥረው የፈለግነውን የሰው ኃይል ለማፍራት ማስቻሉን፣ ከዓለምአቀፍ ሁኔታ ጋር የተስተካከለ መሆኑን፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን ሁኔታ መከተሉን እንዲሁም ወቅታዊ ችግሮችን ፈትቶ ዘላቂ የሆነ ጠንካራ የሰው ሃይል ለማውጣት የሚያስችል መሆኑን የምንገመግምበት በመሆኑ በየወቅቱ ማካሄድ ተገቢ ነው ብለዋል፡፡ እንደ እርሳቸው ገለጻ ከዚህ በፊት በስርዓት ትምህርቱ ተካተው የነበሩት ይዘቶች አሁን አላስፈላጊ ሊሆኑ ይችላሉ፣ አስፈላጊ የሆኑት ደግሞ ያልተካተቱ ስለሚሆኑ የማያስፈለጉትን ለማስወገድ፣ አስፈላጊውን ለመጨመር የስርዓት ትምህርት ፍተሻ ማድረጉ ለነገ የማይባል ተግባር ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የምናወጣው የሰው ሃይል ተፈላጊ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚሆን፣ ያቀድነውን ዓላማ የሚያሳካና የዜጎቻችንን ፍላጎት የሚመልስ ይሆናል ብለዋል፡፡

የስርዓት ትምህርት ፍተሻውን ተቋማዊ ለማድረግም ባለፈው 2006 ዓመት በአንዳንድ ትምህርት ክፍሎች ብቻ ተግባራዊ የሆነው የፕሮግራም ግምገማ ዘንድሮ ሁሉም የትምህርት ክፍሎች ተግባራዊ በማድረግ እያንዳንዱ የትምህርት ክፍሎች ተማሪዎቻቸውን የሚያስመርቁበትን ጊዜ እንዲያቅዱ መደረጉን አቶ ደሳለው አክለው ገልፀዋል፡፡ ለዚህም የጤና ሳይንስ ኮሌጅ በር ከፋች በመሆን እንደሚያግዛቸው እምነታቸውን ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ለስርዓት ትምህርት ፍተሻ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ እንደሚችል ገልፀዋል፡፡



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: misgepower@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

የጤናና ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ የስርዓተ ትምህርት ፍተሻ ሂደት በመጨረሻ አራቱ የትምህርት ክፍሎች የደረሡባቸውን ነጥቦች ሪፖርት የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራሮች በተገኙበት የሚያቀርብ ሲሆን በተገኘው የፍተሻ ውጤት መሰረትም በስርዓተ ትምህርቶች ላይ ማሻሻያዎችን ለማድረግ በየደረጃው በማስፀደቅ ሊያሰራ የሚችልና ሀገሪቱ የምትፈልገውን የሰው ሃይል ለማፍራት የሚያስችል ስርዓተ ትምህርት ለመቅረጽ ያስችላል ተብሏል፡፡ ለዚህም መምህራንና የየትምህርት ክፍል ተጠሪዎች ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክቱ አቶ ጌታቸው እምነታቸውን ገልፀዋል፡፡

ይህን የክለሳ ሂደት የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለሌሎች ኮሌጆችና የትምህርት ክፍሎች ለማውረድ ከጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ጋር በመሆን በቀጣይ እንደሚሰሩ ገልፀዋል፡፡ ኮሌጁ የስርዓተ ትምህርት ፍተሻውን ከ19-23/02/2007 ዓ.ም. ለአምስት ቀናት በፍኖተ ሰላም ከተማ አካሂዷል፡፡

## አዲስ ለተቀጠሩና ከትምህርት ለተመለሱ መምህራን ስልጠና ተሰጠ

በሙሐመድ ሰዒድ

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ2007 ዓም አዲስ ለተቀጠሩና ከትምህርት ለተመለሱ መምህራን ስልጠና ተሰጠ፡፡ ስልጠናውን በንግግር የከፈቱት የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ እንደገለጹት ስልጠናው የመምህራንን የማስተማር ስሜት በማነቃቃት ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ይህ ስልጠና መምህራኑ ወደ ስራ ከመግባታቸው በፊት የሚሰጥ አጭር የትውውቅ ስልጠና መሆኑን ገልጸው በቀጣይ ወራት የተለያዩ ስልጠናዎች በስፋት እንደሚሰጡ ጠቁመዋል፡፡





ዶ/ር ንጉሴ ሥልጠናውን ሲያስጀምሩ

0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: misgepower@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

የዩኒቨርሲቲው የሥልጠና ኦፊሰር አቶ አጽበሃ ገ/እግዚአብሔር እንደገለጹትም ሥልጠናው በሞጁላር የትምህርት አቀራረብ፣ በተከታታይ ምዘና፣ በሚዛናዊ አሰራር ሥርዓት እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ህጎችና ደንቦች ላይ ሰፊ ውይይት ለማድረግ ይረዳል፡፡

እንደ አቶ አጽበሃ ገለጻ ስልጠናው የሚሰጠው አዲስና በትምህርት ላይ የነበሩ መምህራን ናቸው፡፡ በመሆኑም መምህራኑ በማስተማር ሙያ ላይ ጠለቅ ያለ እውቀት እንዲጨብጡ ይረዳል ብለዋል፡፡ እንደ እርሳቸው ገለጻ በሚዛናዊ አሰራር ያልተመራ እንቅስቃሴ ውጤታማ አይሆንም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መምህራን የዩኒቨርሲቲውን ህጎችና ደንቦች ማወቃቸው እቅዶቹን ለማሳካት ይረዳቸዋል፡፡ በመሆኑም ሰልጣኝ መምህራን በንቃት እንዲሳተፉ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡ በቀጣይ ጊዜያትም በቡሬ ግቢ ውስጥ ለሚገኙ አዲስና ከትምህርት ለተመለሱ መምህራን ስልጠና እንደሚዘጋጅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## አዲስ ለተቀጠሩ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጥበቃና ፕሮክተር ሰራተኞች ስልጠና ተሰጠ

በሁሉንአየን ጋሻው

ደ/ማ/ዩ፡- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስርዓተ ፆታ፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና አካል ጉዳተኞች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት አዲስ ለተቀጠሩ የዩኒቨርሲቲው ጥበቃና ፕሮክተር ሰራተኞች በጓደኛዊ አቀራረብ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በግቢው ውስጥ የሁለት ቀናት ስልጠና ሰጠ፡፡



አቶ ሽመልስ አለነ ስልጠናውን ሲሰጡ



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: misgepower@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስርዓተ ፆታ፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና አካል ጉዳተኞች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወ/ሮ ወርቄ ሙሳ እንደገለፁት የስልጠናው ዓላማ በግቢው ውስጥ ከተማሪዎች ጋር በቅርበት የሚሰሩት የጥበቃና ፕሮክተር ሰራተኞች ተማሪዎችን ከችግር ለመከላከልና ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ ጓደኛዊ አቀራረብ ላይ ግንዛቤ ፈጥረው ተማሪዎች የመጡበትን ዓላማ ያለምንም ችግር አሳክተው ለመሄድ እንዲችሉ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት እንዲችሉ ለማስቻል ነው፡፡

ስልጠናውን የሰጡት በስርዓተ ፆታ፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና አካል ጉዳተኞች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ባለሙያ አቶ ሽመልስ አንለይ እና የስርዓተ ፆታ ባለሙያ ወ/ሮ ሰላም መክብብ እንደገለፁት በስልጠናው የዩኒቨርሲቲው የጥበቃና ፕሮክተር ሰራተኞች ስለወጣቶች ባህርያትና ምንነት ግንዛቤ በመፍጠር ለደንበኞቻቸው በጓደኛዊ አቀራረብ የሚፈልጉትን ነገር በአክብሮትና በተገቢው ሁኔታ ለማስተናገድ እንዲችሉ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ብለዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ተማሪዎች አላስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሲፈጽሙ ወይም ለመፈፀም ሲሞክር ሲያዩ ያገኙትን ግንዛቤና የህይወት ተሞክሮ ተጠቅመው ተማሪዎች የመጡበትን የትምህርት ዓላማ እንዲያሳኩ ለማድረግ የበኩላቸውን ድጋፍ ለማድረግ እንደሚያስችላቸው ገልፀዋል፡፡

ስልጠናው፣ ሰልጣኞች ከተማሪዎች ጋር ተግባቦትን በመፍጠር በቅርበት ስለጉዳያቸው በመነጋገርና የመፍትሄ ሃሳቦችን በመስጠት ተማሪዎች የመጡበትን ዓላማ አሳክተው በመመለስ አምራችና ብቁ ዜጐች እንዲሆኑ ለማድረግ እንደሚያስችል ተጠቁሟል፡፡ ተማሪዎች የሚገጥሟቸውን ችግሮች ከሰልጣኞች ጋር በቅርብ በመወያየት ለችግሮቻቸው የመፍትሔ አካል እንዲሆኑም ያስችላል፡፡ ስልጠናው ሰልጣኞችን አሳታፊ በሆነ መልኩ በድራማና በውይይት የተሰጠ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የስልጠናው ተሳታፊ ከነበሩት የፕሮክተር ሰራተኛ የሆነችው ወ/ሪት ማስተዋል ሙሉሰውና የጥበቃ ሰራተኛ የሆነው አቶ ከድር የሱፍ እንደገለፁት ስልጠናው የወጣትነት ባህሪያትና ተግባራትን በተጨባጭ ይገጥማቸው ከነበረው በመነሳት በውይይት ያዳበሩበት በመሆኑ የነበረባቸውን ብዥታ እንደቀረፈላቸውና ለደንበኞች በትህትናና አግባብ ባለው ሁኔታ አገልግሎት ለመስጠትና ተማሪዎች ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር በቀላሉ ለተለያዩ ችግሮች እንዳይጋለጡ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት እንደሚያስችላቸው ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም ለተማሪዎቹ እንደ እህትና ወንድም በመሆን

የሚገጥማቸውን ችግር በጓደኛዊ አቀራረብ አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡

በመጨረሻም አቶ ሽመልስ ዋናው ነገር ሰልጣኞች ስልጠናውን መውሰዳቸው ሳይሆን የወሰዱትን ስልጠና በተግባር በማዋል ተማሪዎችን ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ተያያዥ ችግሮች መከላከል እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡ በስልጠናው ከ80 በላይ የዩኒቨርሲቲው አዲስ ተቀጣሪ የጥበቃና የፕሮክተር ሰራተኞች ከጥቅምት 4-5/2007 ዓ.ም. ድረስ ለሁለት ቀናት ተሰጥቷል፡፡

በተመሳሳይ ዜና ከዚህ በፊት ስልጠናውን የወሰዱ ነባር የፕሮክተርና የጥበቃ ሰራተኞች በስልጠናው ግብዓት አፈፃፀም ላይ የመጣውን ውጤት ለማየት የሚያስችል የግምገማ ውይይት (ሪቪው ሚቲንግ) ከጥቅምት 6-7/2007 ዓ.ም. ተካሂዷል፡፡ በውይይት መድረኩ ላይ እንደተገለፀው የጥበቃና ፕሮክተር ሰራተኞች ስልጠናውን ከወሰዱ በኋላ ተማሪዎች የተለያዩ ችግሮች ሲገጥሟቸው ችግሮቻቸውን በቅርበት እህታዊና ወንድማዊ በሆነ መልኩ በግልጽ ውይይት ለመፍታት እንደቻሉ ጠቁመዋል፡፡ በውይይቱ መጨረሻም በቁጥጥርና ክትትል ስራቸው ላይ የገጠሟቸውን ችግሮች ለማንሳት በ2007 ዓ.ም. የተሻለ ለመስራት የመፈትሔ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡ ለዚህም የጥበቃና ፕሮክተር ሰራተኞች በተማሪዎች ቁጥጥር ላይ በጋራ መስራት እንደሚገባቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ ስለዚህም ከዚህ በፊት የተሰጠው ስልጠና ተገቢና የታሰበለትን ዓላማ ያሳካ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ተማሪዎችን ከተለያዩ ችግሮች ለመከላከልም በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢና ውጭ የተለያዩ የቁጥጥርና ክትትል ተግባራትን ሲያካሂዱ መቆየታቸውን ገልፀዋል፡፡



**ውይይቱ ሲካሄድ**

ከዚህ በተጨማሪ በመድረኩ በስርዓተ ፆታ፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና አካል ጉዳተኞች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት የተሰሩ የዳሰሳ ጥናቶች እንዳሉ የጠቆሙት አቶ ሽመልስ አለነ ጥናቶች ለችግር ተጋላጭ የሆኑትን፣ ምክንያቶችንና ሊወሰዱ የሚገባቸው መፍትሔዎችን አስቀምጠዋል፡፡ እንዲሁም ከቁጥጥር በኋላ የመጣውን ለውጥና የነበረውን ክፍተት አመላክቷል፡፡

በመጨረሻም ወ/ሮ ወርቄ ሙሳ እንዳሉት የተማሪዎች ደህንነትን ለማረጋገጥና ምርታማ ዜጎች ለማድረግ ሁሉም የዩኒቨርሲቲውና የአካባቢው ማህበረሰብ በጋራ ሊሰራ ይገባል ብለዋል፡፡

## ለአዲስ ገቢ የማታ ተማሪዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልእክትና ስለ ኮሌጆች አሰራር ገለፃ ተደረገላቸው

በሰሎሞን አበበ

**ደ/ማ/ዩ፡-** የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለ2007 ዓ.ም. አዲስ ገቢ የማታ ተማሪዎች በኮሌጅ ዲኖች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልክትና ስለ አሰራራቸው ገለፃ ተደረገላቸው፡፡

የገለፃና የእንኳን ደህና መጣችሁ ፕሮግራሙ ዋና ዓላማ ተማሪዎች ለዩኒቨርሲቲው አዲስ በመሆናቸው በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ክፍሎች ማግኘት የሚችሉትን አገልግሎት እውቅና ለመፍጠር፣ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው መከተል ስለሚገባቸው ህጎችና ደንቦች ገለፃ ለማድረግ መሆኑን የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ሬጅስትራር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ገበየሁ ሽፈራው ገልፀዋል፡፡



ኦሬንቴሽን ፕሮግራሙ በተሰጠበት ሰዓት

እንደ አቶ ገበየሁ ማብራሪያ የሬጅስትራር ዳይሬክቶሬቱ በተማከለና ባልተማከለ አሰራር ተደራጅቷል፡፡ የሬጅስትራር ዳይሬክቶሬት ሰራተኞች ተማሪዎችን ተቀብሎ ይመዘግባል፡፡ የተማሪዎችን አካዳሚያዊ መረጃዎች ያደራጃል፣ ያጠናቅራል እንዲሁም የተለያዩ መረጃዎችን

ስቱደንት ኮፒ፣ ዲግሪና ኦፊሽያል ትራንስክሪፕት ለተማሪዎች ይሰጣል፡፡ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ሰዓትም ከ80% እስከ 100% ድረስ በክፍል ውስጥ በመገኘት እንደየኮርሶች ሁኔታ ትምህርታቸውን መከታተል አለባቸው በማለት አሳስበዋል፡፡ አክለውም ተማሪዎች ከ80% እስከ 100% በክፍል ተገኝተው ትምህርታቸውን ካልተከታተሉ የሚከታተሉትን ትምህርት እንዳልተከታተሉ እንደሚቆጠር ገልፀዋል፡፡

ተማሪዎች ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ሰዓት በሚያጋጥማቸው አካዳሚያዊ ጉዳዮች ዙሪያ አማካሪ መምህራኖቻቸውን በመጠቀም ማማከር፣ ኮርሶችን አድ እና ድሮፕ ሲያደርጉም አማካሪ መምህራኖችን በማማከር መፈፀም እንዳለባቸው ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በተለያዩ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች ትምህርታቸውን ሲያቋርጡ ህጋዊ በሆነ መልኩ ዊዝድሮዋል ፎርም በማስፈረም እና መታወቂያቸውን በማስረከብ መሆን አለበት በማለት የሬጅስትራር ዳይሬክተሩ ገልፀዋል፡፡

የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ዲን አቶ ገረመው በበኩላቸው እንደገለፁት በኮሌጁ ባሉት አራት የትምህርት ክፍሎች በማታው ፕሮግራም ለመማር የተመዘገቡት ተማሪዎች ትምህርታቸውን በትጋት በመከታተል ለሀገራችን የኢኮኖሚ እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ አሳስበዋል፡፡

በእንኳን ደህና መጣችሁ ፕሮግራሙ የቴክኖሎጅ ኮሌጅ ዲን አቶ ግርማው እንዳሉት በኮሌጁ ለመማር የተመዘገቡ ተማሪዎች ዘመኑ የቴክኖሎጅ መሆኑን አውቀው ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዲከታተሉና ለሚያጋጥማቸው አካዳሚያዊ ችግሮችም አማካሪ መምህራንን፣ ዲፓርትመንት ተጠሪዎችንና የኮሌጁ ዲኖችን በየደረጃው በመጠቀም መፍታት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

አቶ ጌታቸው ኃይሉ የጤናና ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ ዲን በበኩላቸው የትምህርት አቀራረቡ ሞጁላር እንደሆነ ገልፀው ተማሪዎች አንድ ኮርስ ሲጨርሱ ወደሚቀጥለው ኮርስ እንደሚሸጋገሩ ተናግረዋል፡፡ የጤናና ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪዎች ከሰው ልጅ ህይወት ጋር የተያያዘ ትምህርት ስለሆነ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ዘወትር በመገኘት ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ አሳስበዋል፡፡

በመጨረሻም አቶ ኃይለማርያም ታከለ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ቤተ-መጽሐፍት ተወካይ ኃላፊ ስለ ቤተ-መጽሐፍት አደረጃጀት፣ የአሰራር ሁኔታና በቤተ መጽሐፍቱ ህግና ደንብ ዙሪያ ለአዲስ ገቢ ተማሪዎች ገለፃ አድርገዋል፡፡